# “ሲያልቅ አያምር!”
(ከዳኛቸው ምህረቱ)

የአረብ ልጆች፣ ትምህርት ጠልተው፣
በምኑም በምኑም ተሰላችተው፣
ወደ ትምህርት ቤት፣ አንሄድም ሲሉ፣
አረቦች ልጆቻቸውን፣ “እስራኤል መክራብን!” ይላሉ።

እንደሚባለው የቆዬ፣ አስቂኝ አነጋገር፣
መለስም ማጠፊያው ሲያጥረው፣ ሕዝብን ለማደናገር፣
“ሻዕቢያ ሊወረኝ ነው” ብሎ፣ ይወሻክት ጀመር?
ያውም ባደባባይ፣ “ምንይሉኝን” ሳይጨምር፣
ሃይለማርያም ደሳለኝም፣ ያይጥ ምስክር ድንቢጥ፣
ሁኔታው  ያሳዝናል፣ በአሜሪካ ሲሯሯጥ።

የአራዳ ልጅ እንደሚለው፣ “መለስ ቱሪስት ይብላ፣”
ያረጀ ያፈጀ ነው፣ ይህ ዓይነቱ ተራ መላ።
የኢራኑ ጽንፈኛ ፕሬስ፣ “የእስላም እምቢታ” የሚለው፣
በሰሜን አፍሪካ፣ በአረብ አገር፣ ሲቀጣጠል የሚታየው፣
የሕዝብ ብሶት የወለደው፣ ሕዝባዊ አብዮት ነው፣
በሙባረክም፣ በጋዳፊም፣ አመክንዮ ያልተገታው።

ምን አለ ትንሽ ብታፍሩ? እነመለስ ምን ነካችሁ?
አሜሪካ ከሙባረክ፣ የሚወዳችሁ መሰላችሁ?!

በመልካም አስተዳደር፣ በመከላከያና ደህንነት፣
መቶ ኮሚቴ ቢቋቋም፣ ባሜሪካ ሞግዚትነት፣
የሚያድናችሁ ይመስላችሁዋል?! ከሕዝብ አመጽ፣ ሰደድ እሳት?!
ወይስ ይሆናል መስሏችሁዋል፣ ያለቅጥ በመርበትበት?!
ሉዐላዊት ሀገራችንን፣ የእጅ አዙር ቅኝ ታደርጓት?!

እነመለስ ጨርሳችሁ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ አትናቁ፣
በሻዕቢያ አታመካኙ፣ ሕዝብ ሃያል መሆኑን እወቁ፣
ትንሽ ከታሪክ ተማሩ፣ ጌቶቻችሁን ጠይቁ፣
“የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሆኖ፣ ለጠላት ተጠቅቶ አያውቅም።”
ምኒልክ ያሉትን አስታውሱ፣ ወደዳችሁም ጠላችሁም።
እውነትም ከሆነ የምትሉት፣ አይሆንም እንጅ ከሆነም፣
**ጥለውብን የሄዱትን ዕቃቸውን፣ ቢያነሱልን አንጠላም።**

የምን መርበትበት፣ መደናገር፣
አቅጣጫን ለማስቀየር?
እራሳችሁን አታታሉ፣
የት እንዳላችሁ አስተውሉ።
እንደ ስንቅ አቅማዳ፣ በየቀኑ፣
እያደር አትቅለሉ!